# ምን ተይዞ ጉዞ !!

አገሬ አዲስ

መንገድ ከመጀመር በፊት የሚሄዱበትን ቦታ ማወቅ፣ለምን እንደሚሄዱና እንዴትስ ሊደርሱ እንደሚችሉ ማሰብና ማጥናት ተገቢ ነው።አቅጣጫ መሪ፣ ጠቋሚ መሳሪያና(ኮምፓስ) የካርታ ንድፍ ማዘጋጀትና መያዝ ለጉዞው መሳካት ይረዳል፡፤ መንገድ ስቶ ከመደናበርና አላስፈላጊ ድካም ውስጥ ከመግባት ያድናል።

ሌላው ደግሞ እረጅም መንገድ ሲያስቡ ስንቅ መሰነቅና ሊደርስ የሚችለውን አደጋ አጢኖ ለአደጋው መከላከያ የሚሆን መሳሪያ ማዘጋጀቱም አንዱ ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ነው።የአውሬ ሲሳይ ላለመሆን፣በጎርፍ ላለመጠለፍ ወቅቱንና የከባቢውን ሁኔታ ማወቅ ይጠቅማል። እረጅም መንገድ ለብቻ መጀመር ከማሰብ ይልቅ በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙ ካሉ ፈላልጎ አብሮ መጓዝ ከብዙ ነገር ያድናል።አደጋን በጋራ መቋቋም ይቻላል፣አንዱ ቢደክምና ቢታመም ሌላው ብርታት ይሰጠዋል፤ይጠብቀዋል።አነጋጋሪ መኖሩም መንገዱ ሳይታወቅ እንዲጠቀለል ይረዳል።

ይህ እንግዲህ በተራው የእግር ጉዞ አንጻር፣ከቦታ ወደቦታ ለመንቀሳቀስ ሲታሰብ ሊኖር የሚገባውን ዝግጅት የሚያሳይ ነው።

ወደ ትግል ሜዳም ሲገቡ እንዲሁ ትልቅና እረጅም  ጉዞ ነውና ማንን እንደሚታገሉ፣ከማን ጋር አብረው እንደሚቆሙ፣ምን አሶወግዶ ምን ለማስፈን እንደሆነ  በቅድሚያ በማጥናት እራእይ ነድፎ መወሰን ተገቢ ነው።ጠላትና አጋሩን የማያውቅና ያለዩ፣ዓላማውንና እራእዩን በግልጽ ያላስቀመጠ ድርጅትም ይሁን ስብስብ ለትግል ተነስቻለሁ ቢል ሳይራመድ ባለበት እየረገጠ ወይም  ካሰበበት ሳይደርስ በጠላቱ ቀጭን ብትር ተመትቶ ይወድቃል።

ላለፉት አስርታት ዓመታት በእኛ በኢትዮጵያውያን ትግል ውስጥ ተደጋግሞ የታየውና የደረሰው ውድቀት ከዚህ የመነጨ ነው።የዓላማ ጥራትና ጥናት አለመኖር፣ጠላትና ወዳጅን ለይቶ አለማወቅ፣የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ብሎ ተግበስብሶ መጓዝ፣ወገንተኛነት፣የግልና የቡድን ጥቅምን አብልጦ ማየት፣ከሚመሳሰሉት ጋር በጋራ አለመቆም፤ደፍሮ አለመጠየቅ፤በጭፍኑ ደግፎ ማጨብጨብ፣ወረተኛነት….

እነዚህ በተደጋጋሚ የታዩ ድክመቶች ለረጅም ጊዜ የተደረገውን ትግልና የተከፈለውን መስዋእትነት ዋጋ ቢስ ያደረጉ መሆናቸውን ልንክድ አይገባም።እርግጥ ነው በታጋዩ ድክመት ላይ የጠላት የገንዘብና የመሳሪያ ጥንካሬ ተጨምሮበት የሚደርሰው ስብራት ቀላል አይደለም።ሁል ጊዜ ችግርና ድክመትን እያነሱ ፣በዛው በተለመደው የትግል ባህል ከመጓዝ ይልቅ ከዚያ አይነቱ ተደጋጋሚ ጥቃት እንዴት መዳንና ለታሰበው ድል መብቃት ይቻላል የሚለውን ጥያቄ አንስቶ መፍትሔ መፈለግ ተገቢ ነው።

ላለፉት ሃያ ስድስት ዓመታት በተለይም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደው ትግል አገር በመበታተንና አገር በማዳን ፣በጎሳ ፖለቲካና በአገር አቀፍ ፖለቲካ፣በአክራሪና በለዘብተኛ  የእምነት ተከታዮች መካከል ነው።በአሰላለፍ ደረጃ ከታዩ

ለኢትዮጵያ አንድነት፣አገር አቀፍ ፖለቲካን የሚያራምዱና በእምነት ለዘብተኛ አቋም ያላቸው በአንድ ላይ ሊሰለፉ የሚችሉ ሲሆኑ የሚታገሏቸውም፣ጸረ አንድነት ሃይሎችን፣ የጎሳን ፖለቲካ የሚያራምዱ ጠባቦችን፣የሃይማኖት አክራሪዎችን ይሆናል።

በአለፉት አስርታት ዓመታት የታየው አሁንም የሚታዬው ድክመትና ለችንፈት ምክንያት የሆነው አካሄድ እነዚህን አጥፊና ጠፊ የሆኑ አመለካከቶችና ሰልፎች በአንድ ተራ ለመደርደር መሞከሩ ነው። እነዚህ የተለያዩ ዓላማና ፍላጎት ያላቸው ቡድኖችም ሆኑ ስብስቦች ተመካክረው አንድ ይሆናሉ ወይም ለአንድ ዘላቂ ዓላማ ይቆማሉ ማለት ዘበት ነው። ያለውን ስርዓት ለመጣል ፍላጎታቸው አንድ ስለሆነ በስልት ደረጃ ለመተባበር ቃል ሊገቡ ይችላሉ ከዚያ በኋላ ለማስፈን የሚፈልጉት ስርዓትም ሆነ ለውጥ እንደዓላማቸው የተራራቀ ስለሆነ መልሰው ከግጭት አዙሪት ውስጥ የሚገቡበት ዕድሉ ሰፊ ነው።

ለአንዴም ሆነ ለዘለቄታው አሁን የሰፈነው አገር አጥፊ አስተሳሰብና አሰላለፍ ተወግዶ ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድትኖር ከተፈለገ የኢትዮጵያን መኖር የሚሹ፣በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ፣አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ ፣አንድ ሰንደቅ ዓላማ ብለው ለእኩልነትና ለዴሞክራቲክ ስርዓት መስፈን የሚታገሉ ብቻቸውን ጎራ ለይተው መሰባሰብ ይኖርባቸዋል። ከጎሳ ፖለቲካ አቀንቃኞች በተለይም የወያኔን ህገ መንግስት አወዳሽና ተቀባይ ከሆኑት ጋር በምንም መልኩ ቢሆን አብረው ሊሰለፉ አይገባቸውም፤በመካከላቸው ሰፊ ልዩነት ስላለ አጋር ሊሆኑ አችሉም። እናቀራርባለን ብሎ መታከት ባለፉት አመታቶች የተደረገውን ስህተት መድገም ይሆናል።ለዚያም ነው በጽሁፉ መጀመሪያ ላይ ስለጉዞና ትግል ሲታሰብ በቅድሚያ መሟላት የሚገባውን በአጭሩ ለመግለጽ የተሞከረው።

አሁን በየቦታው የተቀጣጠለው ሕዝባዊ ትግል ውጤታማ እንዲሆን ከአካባቢ ወጥቶ አገር አቀፍ መልክ ሊያዝ ይገባዋል።የጎንደር፣የጎጃም፣የወሎ፣የሸዋ፣አገር ወዳዶች ትግል ከሌላው ክፍለሃገር ተወላጅና ኑዋሪ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ትግል ጋር መያያዝ አለበት።አገርን ከመበታተን አድኖ ለተሻለች ኢትዮጵያ፣ ለዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት ለሰፈነባት ኢትዮጵያ፣የጎሳና የእምነት አክራሪዎች የማይፈነጩባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ከዚህ የተሻለ አካሄድ አይኖርም። ጠንክረው ሲቆሙ ብቻ ነው ተሰሚነትና ተከባሪነት የሚኖረው። በተዝረከረከ መልኩ እንኳንስ ከጠላት ከወዳጅም በኩል መከበር አይታሰብም።በተጨማሪም ግልጽነት ወሳኝ ነው።

ህብረብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች አቋማቸውን ግልጽ ሊያደርጉ ይገባል፤አገር ሳይኖር ስርዓት ማስፈን አይኖርምና ከአገር ወዳዱ ሕዝባዊ ትግል ጋር አብረው መሰለፍ ይኖርባቸዋል።የተጀመረውን ሕዝባዊ ትግል በማቀናጀት፣በማገዝና የጋራ አመራር በመስጠት ተግባር ላይ ሊሰለፉ ይገባል።መጀመሪያ የመቀመጫየን እንዳለችው ቅድሚያ ለአገር አንድነት መስጠት ይገባል።ስልጣን ለመያዝ ይረዳኛል በማለት ለአገሪቱ ሰላምና አንድነት የማይጠቅሙ እንደውም የአደጋው ተሸካሚ የሆኑትን ሃይሎች ማግበስበስ ካለው ስርዓት ባለቤቶች የተለዩ አያደርግም።

ወያኔን በመቃወም ብቻ ነፍጥ ማንሳት የለውጥ ዋስትና አይሆንም።በዚህ መልክ የሚመጣ ለውጥ ቢኖር የጅራፍ ለውጥ ይሆናል።የዚህ አይነቱ አዝማሚያ ሰፊውን ሕዝብ ውዥንብር ውስጥ የከተተ ሲሆን በአገራቸው ዱር ጫካ የተሰማሩትን አገር ወዳዶችም ለአደጋ አጋልጧቸዋል።ሊደርስላቸው የሚገባውን እርዳታና ድጋፍ አመንምኖታል።የተቀጣጠለው ሕዝባዊ ትግል

ካልተጠናከረና ፈር ካልያዘ ሊዳከም ብሎም ሊጠፋ ይችላል።ያ ከሆነ ደግሞ ወያኔና ግብረአበሮቹ ለዳግመኝ ጥቃትና የስልጣን ዘመን ዕድል አገኙ ማለት ነው።አገሪቱንም ወደ ፈለጉት አቅጣጫ ሊወስዷት ይችላሉ። የመበታተኑም አደጋ እውን ይሆናል።

የፖለቲካ ድርጅቶች መስመራቸው፣የሊበራል፣የሶሻሊስት ወይም የዴሞክራት ሊሆን ይችላል፤ያ ደግሞ ከወያኔ መወገድ በኋላ ለሕዝብ ምርጫ የሚቀርብ ጉዳይ ነው።ለመስመራቸው ቅድሚያ እየሰጡ አለመተባበር ከፈረሱ ካሮሳውን ማስቀደም ይሆናል።

አጥፊና ጠፊ የሆኑትን አዞና አሳ በአንድ ላይ ማርባት አይቻልም።አገር ወዳድና ጎሰኛ አገር አፍራሽም እንደዚሁ የትግል አጋር ሆነው አንድ ላይ ሊቆሙ አይችሉም።አንዱ በአንዱ የሚወገድ እንጂ ጎን ለጎን አብሮ የሚኖር አይደለም። አሁን በውጭ አገር በልዩ ልዩ ስም ተበታትነው የሚባክኑት ህብረብሔር የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ሚናቸውን ለይተው የሚተባበሩበት የጋራ ጉባኤ ነገ ዛሬ ሳይሉ በአስቸኳይ አካሂደው አገር አድን የጋራ አመራር ፈጥረው የአገርቤቱን ሕዝባዊ ትግል ማገዝ ይኖርባቸዋል። ለዚያ የማይተባበር ድርጅት ካለ የድጋፍ ተአቅቦ ሊደረግበት ይገባል።ይህን ሳያደርጉ በቃላት ብቻ ለውጥና ዴሞክራሲ እያሉ መጮህ ለለውጥ የቆሙ አያደርጋቸውም፤ስለተመኙ ብቻ ለውጥም ሊመጣ አይችልም ።እርስ በርስ የሚጠላለፉ ከሆነ ይበልጥ ሕዝቡ ተስፋ እንዲቆርጥ ያደርገዋል።

በአገር ቤቱ ትግል ውስጥ ለልዩ ልዩ ዓላማ የተሰለፉ ስብስቦች ስላሉ ሁሉንም በአንድ ዓይን ማየትና የሕዝባዊ ትግል አካሎች አድርጎ መቁጠርም ስህተት ነው። ለአገሪቱ አንድነትና ሰላም ደንታ የሌለው፣በውጭ አገር እርዳታ ስልጣን እይዛለሁ ወይም እገነጥላለሁ ብሎ የሚቋምጠውን ስብስብ የሕዝባዊ ትግሉ አካል ሳይሆን ጠላት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።

ዓላማና ግቡን፣ መነሻና መድረሻውን፣ወዳጅና ጠላቱን በቅጡ ለይቶ የሚያውቅ የትግል ጎራ ለሚያስበው ድል ይበቃል።የዚያ ባለቤት ያልሆነው ግን እታገላለሁ ቢል ምን ተይዞ ጉዞ!ነውና ለድል መድረሱ ብቻ ሳይሆን ለትግል መነሳቱም አጠራጣሪ ይሆናል።

የኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ግንባር ይመስረት!! ተግበስብሶ መንጎድ ይብቃ!!አንድ አገር፣አንድ ሕዝብ፣አንድ ሰንደቅ ዓላማ!!!

አገሬ አዲስ

http://www.ethiopanorama.com